*AMHARIC*

# የሜትሮ አውቶቡስ ትራንስፖርት ለባላርድና ፍራንክሊን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች

ከሰብተምበር 2006 አመተ ምህረት ጀምሮ የባላርድና የፍራንክሊን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች የከተማ ሜትሮ አውቶቡስ መጠቀም ይጀምራሉ።እንደ ሌሎች ብዙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ካሁን ጀምሮ ወደ ት/ቤት ለመሄድ የሜትሮ አውቶቡስ መጠቀም ይጀምራሉ ማለት ነው።

## የሜትሮ አውቶቡስ ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ የሆነ ማን ነው?

የባላርድና ፍራንክሊን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሆኑ ሁሉ የሚኖሩበት አድራሻ ከትምህርትቤቱ ከ2.5 ማይል ርቀት በላይ ከሆነ የሜትሮ አውቶቡስ ተጠቃሚ ለመሆን ብቁ ይሆናሉ።

ተማሪው በልዩ ትምህርት ፕሮግራም IEP የሚማር ከሆነ ልዩ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል። ተማሪው በ504 ተባሎ በሚጠራው ፕላን ውስጥ ከሆነም በፕላኑ መሰረት የማያቋርጥ የትርንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል።

## ይህ ለውጥ ለማድረግ ለምን አስፈለገ?

ይህ ፕሮግራም በተለይ ለባላርድና ፍራንክሊን ሁለተኛ ደረጃ ትምህረትቤት ተማሪዎች ለሙከራ ተባሎ የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው።የሜትሮ አውቶቡስ በመጠቀም ብዙ የገንዘብ ትርፍ ከተገኘበት ፕሮግራሙ ወደ ሌሎች ት/ቤቶች እንዲስፋፋ ይደረጋል።

ትምህርትቤቶች ትምህርት የሚጀምሩበትና የሚጨሩስበት ተለዋዋጭ የሆነ ሰአት ይኖራቸዋል ማለት ነው። ይህ ማለት መጪው አመት ትምህርት ዘግይተው ይጀምራሉ ማለት ነው።ለምሳሌ የባላርድ ትምህርትቤት የትምህርት ሰአት ከ8፤20 እስከ 2፤50 ሲሆን የፍራንክሊን ደግሞ ከጥዋቱ 8፤00 እስከ 2፤30 ይሆናል ማለት ነው።

ተማሪዎች ወደ ትምህርትቤት አስቀድመው በጥዋቱ የመሄድ ወይም በትምህርቤቱ አንዳንድ ስራዎች ለመሳተፍ እዛ ለመቆየት ብዙ አማራጭ ይኖራቸዋል ማለት ነው

ተማሪዎች ወደ ትምህርትቤት ለመሄድና ከትምህርትቤት ለመምጣት ብዙ አማራጭ ይኖራቸዋል ማለት ነው።

## ተማሪዎች የትኛው አውቶቡስ ነው የሚይዙት?

በሰብተምበር ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ብቁ ለሆኑለሁሉም ተማሪዎች(ከት/ቤቱ ከ2.5 ማይል ርቀት ለሚኖሩ ተማሪዎች) በአድራሻቸው ስለ የሜትሮ አውቶቡስ በምትኖሩበት አድራሻ መሰረት አውቶቡሱ የሚመጣበትና የሚሄድበት ጊዜና ሰአቶች የሚገልጽ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች ይላክላቸዋል።

## ተማሪው ለጉዞው የሚከፈለው ክፊያ እንዴት መክፈል ይችላል?

ብቁ የሆኑ ተማሪዎች(ከ2.5 ማይል ርቀት የሚኖሩ) ወደ ትምህርትቤት ለመመላለስ የመጠቀሙበት የሜትሮ የወር ነጻ ትኬት ይሰጣቸዋል።

በሰብተምበር ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የመጀመሪያ ትምህርት የሚጀመርበት ቀን ወደ ትምህርት ቤት እንዲጓዙበት የሜትሮ አውቶቡስ ትኬት ብቁ ለሆኑ (ከ2.5 ማይለ ርቀት በላይ ለሚኖሩ) ለሁሉም ተማሪዎች በአድራሻቸው ይላክላቸዋል።ከዛ ተማሪዎች የወሩ ነጻ ትኬት ከትምህርትቤቱ ማግኘት ይችላሉ።

ነጻ የሜትሮ አውቶቡስ ትኬት በማንኛውም ጊዜና ሰአት በሁሉም የሜትሮ ትራንዚት አውቶቡስ ሁሉ በነጻ ለመጓዝ ይችላሉ።

ነጻ የሜትሮ ትኬት ያላቸው ተማሪዎች በኮሚዩኒቲ ትራንዚት፣ ኤቨሬት ትራንዚት፣ ፒሬስ ትራንዚትና ሳውንድ ትራንዚት እንዲሁም ኤክስፐረስና ሳውንድ ኮሚዩተር ባቡር ተጨማሪ 50 ሳንቲም በመክፈል ለመጓዝ ይችላሉ።

## ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት ማንን ለማነጋገር እንችላለን?

ማንኛውም ጥያቄ ካላችሁ የባይሊነጓል ማእከልን በሚከተለው ስልክ ቁጥር ሰልክ በመደውል መጠየቅ ትችላላችሁ (206) 252-7750.

<u>*AMHARIC*</u>

## <u>የሜትሮ አውቶቡስ ነጻ ትኬት አጠቃቀም</u>

የሜትሮ ነጻ ትኬት በምትቀበሉበት ጊዜ በትርንዚትና/ስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች የሜትሮ አውቶቡስ አጠቃቀም ህግና ደንብ እንደምታከብሩ ትስማማላችሁ

**ለሁሉም የሜትሮ ተሳፋሪ ደህንነት:**
**ማንኛውም ሰው ተገቢውን ክፍያ ከከፈለ የሜትሮ አውቶቡስ መጠቀም ይችላል፡፤**
**ማንኛውም የሜትሮ ተሳፋሪ የሌሎች ተሳፋሪዎች መብት ማክበር አለበት።**
**በአውቶቡስ ውስጥ ተሳፋሪዎች ሊከተሉት የሚገባ ህግና ደንብ አላቸው**
**ህጉም በሎካልና በሜትሮ ትራንዚት ፖሊስ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል**

**ማናቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባር የሰራ ሰው በወንጀል ይከሰሳል፤ ሊታሰር ወይም ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል**

- ተገቢውን ክፍያ አልከፍል ማለት
- አልከሆል መጠጥ መጠጣት
- ካለ የጆሮ ማዳመጫ ሬድዮ ወይም ቴፕ ማዳመጥ
- መተኛት ወይም ከአንድ ወንበር በላይ መያዝ
- ሹፌሩን ወይም ሌላ ተሳፋሪ መሳደብ
- መደባደብ
- ማቆሸሽ ወይም ማበላሸት
- ንብረት ማውደም
- መተላለፊያ መንገድ መዝጋት
- ስጋራ ማጤስ
- የሚቀጣጠል ነገር መያዝ
- መትፋት
- መንጠላጠል ወይም መዝለል
- በመስኮት ወይም በበር የሰውነት አካል ማውጣት

**ስለ ሜትሮ አጠቃቀም ህግና ደንብ ተጨማሪ ዝርዝር ጽሁፍ ከሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል:**
*County Clerk of the Council offices*
*King County Courthouse Room 402*
*516 Third Avenue*
*Seattle, Washington 98104-2386*
**እንዲሁም በሁሉም መጽሃፍት ቤቶች**

**ህጉንና ደንቡን የጣሰ ሰው የነጻ ትኬቱ እንዲነጠቅ ይደረጋል**

**ከላይ የተጻፈው ህግና ደንብ አንብቤ ተረድቻለሁ**

**የተማሪው ፊርማ** ______________________ **ሙሉ ስም** ____________________

**ቀን** ____________________